## ትምህርት 20

ጥያቄ 50:- እግዚአብሔር አብ ሰዎችን ለማዳን ምን አደረገ?

መልስ:- እግዚአብሔር አብ ሰዎችን ለማዳን አንድያ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ስለ ሰው ኃጢአት እንዲሞት ወደዚህ ዓለም ላከው፤ ዮሐ.3:16::

ጥያቄ 51:- የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምን ዓይነት መንገድ ወደዚህ ዓለም መጣ?

መልስ:- የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ተፀንሶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ሰው ሆኖ ወደዚህ ዓለም መጣ፤ ሉቃ.1:35::

ክርስቶስ ወደ ዓለም መጣ፤ ሉቃ.1-2

ሀ/ እግዚአብሔር አብ ሰዎችን ለማዳን ምን አደረገ?
1/ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት የምንድንበትን መንገድ አቀደልን፤ ዘፍ.3:15፤ የሐዋ.2:23::
2/ ወደደን፤ ሮሜ 5:8::
3/ ልጁን ወደዚህ ዓለም ላከው፤ ዮሐ.3:16::

ለ/ የክርስቶስ ልደት:-
1/ በመንፈስ ቅዱስ ስለ ተፀነሰ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፤ ማቴ.1:20፤ ሉቃ.1:35::
2/ ከድንግል ማርያም ስለተወለደ ሥጋን ለብሶ ሰው ሆነ፤ ሉቃ.1:31፤ 34-35::

ሐ/ ክርስቶስ ለምን ሰው መሆን ነበረበት?
1/ ድካማችንን እንዲያውቅ ሰው መሆን ነበረበት:: እንደኛ ተፈተነ÷ ተራበ÷ ተጨነቀ፤ ዕብ.4:15::
2/ የሰውን ኃጢአት እንዲሸከም ሰው መሆን ነበረበት::
3/ የኃጢአትን ዋጋ ለመክፈል መሞት ነበረበት:: እግዚአብሔር ስለማይሞት ለመሞት ሰው መሆን ነበረበት::
4/ አዳምና ሔዋን ኃጢአት በሠሩ ጊዜ እግዚአብሔር የተናገረው ትንቢት እንዲፈጸም ከሴት መወለድ ነበረበት፤ ዘፍ.3:15::

መ/ ኢየሱስ ፍጹም እግዚአብሔር ነው::
1/ የአዳምን ኃጢአት እንዳይወርስ ከድንግል ማርያም በመንፈስ ቅዱስ እንጂ ከአዳም ዘር አልተወለደም ነበር::

2/ የኃጢአታችንን ዋጋ እንዲከፍል ንጹሕና ኃጢአት የሌለበት መሆን ነበረበት። ኃጢአት የሌለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።
3/ ሞትን አሸንፎ ከሞት መነሣት የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው።
4/ በኢሳይያስ 9፡6 የተነገረውን ትንቢት የሚፈጽም እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ሠ/ ከዳዊት ዘር ተወለደ።
1/ በትንቢት እንደተነገረ የዳዊት ልጅ ነው፤ ሉቃ.1፡32።
2/ በትንቢት እንደተነገረ በዳዊት ከተማ በቤተ ልሔም ተወለደ፤ ሚክ.5፡2፤ ሉቃ.2፡3-5። እግዚአብሔር ዮሴፍና ማርያም ከናዝሬት ወደ ቤተልሔም እንዲሄዱ ንጉሡ አውግስጦስ አዋጅ እንዲያወጣ አደረገው።

ረ/ ኢየሱስ ለምን ተወለደ?
ገብርኤል ምክንያቱን ሲገልጽ፦ «ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋል» አለ፤ ማቴ.1፡21። ኢየሱስ ብዙ ትምህርት አስተማረ፥ ብዙ ታምራት ሠራ። ነገር ግን የመጣበት ዋናው ምክንያት እኛን ከኃጢአታችን ለማዳን ነው።

## ትምህርት 21

ጥያቄ 52፦ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውን ከኃጢአቱ እንዴት ሊያድነው ቻለ?
መልስ፦ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ኃጢአት ተሸክሞ በሰው ምትክ በመስቀል ላይ በመሞት፥ በሶስተኛው ቀን በመነሣትና ወደ ሰማይ በማረግ ሰውን ከኃጢአቱ ሊያድነው ቻለ፤ 1ጴጥ.2፡24።

ጥያቄ 53፦ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን ሥራው ምንድነው?
መልስ፦ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን ሥራው በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ለአማኞች ዘወትር ማማለድ ነው፤ 1ጢሞ.2፡5፤ ዕብ.4፡15-16።

### ክርስቶስ ሰውን እንዴት አዳነ?

ሀ/ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሞቱ ሰውን አዳነ።
1/ ትንቢትን ለመፈጸም በመስቀል ላይ ሞተ፤ ዮሐ.3፡14-15።
2/ ክርስቶስ ቅዱስ ስለነበረ ስለ ሰዎች ኃጢአት እንጂ ስለ ራሱ ኃጢአት አልሞተም። የሰውን ኃጢአት በመሸከም ጽድቁን ለሰው ሰጠ፤ 2ቆሮ.5፡21።
3/ ክርስቶስ የሰውን ኃጢአት በመስቀል ላይ ተሸክሞ በመሞቱ የኃጢአትን ዋጋ ከፈለ፤ ኢሳ.53፡6፤ ሮሜ 6፡23።
4/ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል፤ 1ዮሐ.1፡7።

ለ/ ሞትን አሸንፎ በመነሣቱ ሰውን አዳነ።

1/ ክርስቶስ ሞትን አሸንፎ በመነሣቱ አማኞችን አጸደቀ፤ የኢየሱስ ትንሣኤ እግዚአብሔር ስለኃጢአታችን የሞተውን የኢየሱስን መሥዋዕትነት እንደተቀበለ ያሳያል፤ ሮሜ 4:24-25፤ 1ቆሮ.15:17።
2/ እርሱ ከሞት እንደተነሣ አማኞችም ከሞት ይነሣሉ፤ 1ቆሮ.15:22።
3/ ክርስቶስ ከሞት ተነሥቶ ለአማኞች አዲስ ሕይወት ሰጠ፤ ሮሜ 6:4፤ ኤፌ.2:5።

ሐ/ ክርስቶስ ወደ መንግሥተ ሰማያት በማረጉ ሰውን አዳነ።
1/ በአባቱ ቀኝ ተቀምጦ ስለኛ ይማልዳል። ሊቀ ካህናችን ነው፤ ዕብ.4:15-16፤ 1ጢሞ.2:5፤ ዕብ.7:25።
2/ የቤተ ክርስቲያን ራስ ስለሆነ እኛን ደግሞ ወደ እርሱ እንደሚያደርሰን ያረጋግጥልናል፤ ኤፌ.1:21-23፤ 2:6-7።
3/ ሄዶ ቦታ ካዘጋጀ በኋላ እርሱ በሚኖርበት እኛም በዚያ እንድንኖር ተመልሶ መጥቶ ይወስደናል፤ ዮሐ.14:3።
4/ እርሱ ስለ ሄደ መንፈስ ቅዱስን በምትኩ ላከልን፤ ዮሐ.16:7።

## ትምህርት 22

ጥያቄ 54:- ሰው ከዘላለም ሞትና ፍርድ እንዴት ይድናል?
መልስ:- ሰው ንስሐ በመግባትና ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ መድኃኒቱ በመቀበል ከዘላለም ሞትና ፍርድ ይድናል።

### ሰው ለመዳን ምን ማድረግ ያስፈልገዋል?

ሀ/ ንስሐ መግባት ያስፈልገዋል፤ ማቴ.4:17፤ የሐዋ.2:38፤ 20:20-21።
1/ ኃጢአተኛ መሆኑን ተረድቶ ኃጢአቱን ለመተው ፈቃደኛ መሆን አለበት፤ ሮሜ 3:23፤ የሐዋ.3:19-20።
2/ ስለ ሠረው ኃጢአት ተጸጽቶ ኃጢአቱን ትቶ መንገዱን መለወጥ አለበት፤ ምሳሌ 28:13፤ ኢሳ.55:6-7።

ለ/ ራሱን ማዳን እንደማይችል ማወቅ ያስፈልገዋል።

ሐ/ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሞቱ ለሰው ጸፃንነት የሚያስፈልገውን ሁሉ ስለፈጸመ ሰው ክርስቶስን እንደ ግል መድኃኒቱ መቀበል ያስፈልገዋል።
1/ ዳግመኛ መወለድ አለበት፤ ዮሐ.3:3። ዳግመኛ የሚወለደው ከመንፈስ እንጂ ከሥጋ አይደለም፤ ዮሐ.3:6። እናትና አባቱ አማኞች ቢሆኑም ልጁ ራሱ ዳግመኛ መወለድ አለበት። ዳግመኛ ተወልዶ የእግዚአብሔር ልጅ መሆን የሚችለው ክርስቶስን ሲቀበል ብቻ ነው፤ ዮሐ.1:12-13።

1/ ዮሐ.3:16፤36:- በክርስቶስ የሚያምን የዘላለም ሕይወት እንዳለውና እንደማይጠፋ ይገልጻል::
2/ ዮሐ. 3:18:- በክርስቶስ በሚያምን እንደ ማይፈረድበት ይገልጻል::
3/ ዮሐ.5:24:- በክርስቶስ የሚያምን የዘላለም ሕይወት እንዳለውና ከሞት ወደ ሕይወት እንደተሻገረ ይገልጻል::
4/ 1ዮሐ.5:12:- ልጁ ያለው ሕይወት እንዳለው ይገልጻል::
5/ ኢየሱስ:- «እኔ የዘላለምን ሕይወት እሰጣቸዋለሁ፥ ለዘላለም አይጠፉም፥ ከእጄ ማንም አይነጥቃቸውም» ይላል፤ ዮሐ.10:28::

ሐ/ ሰው የዘላለም ሕይወት እንዳለው መንፈስ ቅዱስ ይመሰክርለታል::
1/ መንፈስ ቅዱስ ከሰውዬው መንፈስ ጋር ሆኖ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ይመሰክርለታል፤ ሮሜ 8:16::
2/ መንፈስ ቅዱስ ለአማኙ የልጅነትን መንፈስ ይሰጠዋል፤ ሮሜ 8:15::
3/ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ልጆች ይመረቸዋል፤ ሮሜ 8:14::
4/ መንፈስ ቅዱስ አማኙ የእግዚአብሔር ልጅ እንዲሆን ያትመዋል፤ ኤፌ.1:13-14፤ 4:30::
5/ መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ልብ ውስጥ የጀመረውን ሥራ ለመፈጸም ይችላል፤ ፊልጵ.1:6፤ ይሁዳ 24-25::

መ/ አማኙ ጸንነቱን እንዲጠራጠር የሚያደርጉ ነገሮች:-
1/ አማኙ ኃጢአት ሲሠራ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ኅብረት ለጊዜው ይቋረጣል፤ «ኃጢአት ስለሠራሁ የእግዚአብሔር ልጅ አይደለሁም» ብሎ ሊፈራ ይችላል:: በኃጢአቱ ቢናዘዝ ግን እግዚአብሔር ይቅር ይለዋል፤ 1ዮሐ.1:9፤ 2:1::
2/ ሰይጣን አማኙን ሊከሰውና ሊያጠራጥረው ይሞክራል፤ ራእይ 12:10::

ሠ/ ስለ ጸንነት ማረጋገጫዎች የተሳሳተ አመለካከት፤
1/ «የዘላለም ሕይወት አለኝ፤ ስለዚህ ኃጢአት ብሠራ ምን አለ?» የሚል ሰው ተሳስቷል:: በእውነት የክርስቶስ ልጅ ቢሆን ኖሮ እንደዚህ አያስብም ነበር፤ ሮሜ 6:1-3፤ 15-19፤ 1ዮሐ.5:18::
2/ እያንዳንዱ ሰው እውነተኛ እምነት እንዳለው ራሱን ይመርምር፤ 2ቆሮ.13:5:: እውነተኛ አማኙ ኃጢአት ሲሠራ ስለኃጢአቱ ተጸጽቶ ይናዘዛል::

## ትምህርት 24

ጥያቄ 55:- ክርስቶስ ከመሞቱ በፊት ሰዎች ከኃጢአት እንዴት ይድኑ ነበር?
መልስ:- ክርስቶስ ከመሞቱ በፊት በሚመጣው መድኃኒት በማመን ከኃጢአት ይድኑ ነበር።

ጥያቄ 56:- ክርስቶስ ከመሞቱ በፊት ሰዎች እምነታቸውን በምን ይገልጹ ነበር?
መልስ:- ክርስቶስ ከመሞቱ በፊት ሰዎች የእንስሳ መስዋዕታቸውን በእግዚአብሔር መሠዊያ ላይ በማቅረብ እምነታቸውን ይገልጹ ነበር።

ጥያቄ 57:- የእንስሳ መሥዋዕት ሊያድናቸው ይችል ነበር?
መልስ:- የእንስሳ መሥዋዕት በኃጢአተኞቹ ፈንታ የሚሞተው የእግዚአብሔር በግ የክርስቶስ ምሳሌ ነበረ እንጂ ሊያድናቸው አይችልም ነበር፤ ዕብ.10:4

### መሥዋዕት የክርስቶስ ምሳሌ መሆኑ

በብሉይ ኪዳን ጊዜ እግዚአብሔር መንፈሳዊ ትምህርትን ለሰዎች በምሳሌ እንዳስተማረቸው የደኅንነትንም መንገድ ደግሞ በመሥዋዕት ምሳሌ አስተምሮቸዋል።

ሀ/ ለመሥዋዕት የሚያቀርቡት እንስሳ:-
1/ ወንድ መሆን ነበረበት፤ ዘሌዋ.1:3:- ኢየሱስ ወንድ ነበረ።
2/ ነውር የሌለበት ንጹሕ መሆን ነበረበት። ኢየሱስ ኃጢአት የሌለበት ነበረ።

ለ/ የመሥዋዕት አቀራረብ ሥርዓት:-
1/ መሥዋዕቱን ያቀረበው ሰው ባቀረበው እንስሳ ራስ ላይ እጁን ጭኖ ኃጢአቱን ይናዘዛል፤ ዘሌዋ.1:3-4። ስለኃጢአቱ ተጸጽቶ ኃጢአቱን በእንስሳው ላይ ያኖራል ማለት ነው። እንደዚሁም እግዚአብሔር የእኛን ኃጢአት በክርስቶስ ላይ አኖረ፤ ኢሳ.53:6፤ 1ጴጥ.2:24።
2/ የኃጢአት ዋጋ ሞት ስለሆነ እንስሳው በሰውዬው ፈንታ ይሞት ነበር፤ ሮሜ 6:23፤ ዘሌዋ. 1:5። የበጉ ደም ለጊዜው ኃጢአቱን ይሸፍን እንጂ ኃጢአቱን ሊያስወግድ አይችልም ነበር፤ ዕብ.10:4። ክርስቶስ ግን የእግዚአብሔር በግ ሆኖ በመሞቱ ኃጢአታችንን በሙሉ አስወገደልን፤ ዮሐ.1:29።

ሐ/ የሊቀ ካህናት ሥራ:-

1/ ሊቀ ካህኑ የእንስሳውን ደም ይዞ ታቦቱ ወዳለበት ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ገብቶ በታቦቱ ላይ ደሙን ይረጭ ነበር:: ክርስቶስ የኛ ሊቀ ካህን ሆኖ የራሱን ደም ይዞ በቀጥታ እግዚአብሔር ወዳለበት ገባ እንጂ በሰው እጅ ወደተሠራ ቤት አልገባም፤ ዕብ.9:11-12፤24::

2/ በብሉይ ኪዳን ጊዜ በየዓመቱ ካህናት መሥዋዕትን ማቅረብ ነበረባቸው፤ ዕብ. 10:1:: ሲያቀርቡ በምሳሌ የኢየሱስን መምጣት ያሳስቡ ነበር:: አሁን ከብት አርደን ደሙን ማቅረብ አያስፈልገንም:: ኢየሱስ በመጣ ጊዜ ምሳሌውን ፈጽሞ አንድ ጊዜ ብቻ በመሞቱ ኃጢአታችንን በሙሉ አስወግዷልናል፤ ዕብ.9:28::

3/ በብሉይ ኪዳን ጊዜ ሊቀ ካህኑ ብቻ ደም ይዞ መጋረጃውን አልፎ ታቦቱ ወዳለበት ለመግባት ይችል ነበር:: ክርስቶስ በተሰቀለ ጊዜ መጋረጃው ስለተቀደደ አሁን እኛ በኢየሱስ ደም ወደ እግዚአብሔር ለመምጣት እንችላለን፤ ማቴ. 37:51፤ ዕብ.10:19-20::

መ/ እኛ ዛሬ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደም በማመን እንደምንድን ሁሉ በብሉይ ኪዳን ጊዜም ሰዎች በእምነት መሥዋዕት ሲያቀርቡ በሚመጣው ክርስቶስ በማመን ይድኑ ነበር::

### የክፍል አምስት ጥያቄዎች

1/ ሕግን በመጠበቅ ሰው ለመዳን እንደማይችል የሚያስረዱ ሁለት ጥቅሶችን ጥቀሱ::

2/ ሮሚ 4:1-5 ምን ያስተምረናል?

3/ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ ወደዚህ ዓለም ባይመጣ ኖሮ ሰውን ለማዳን ይችል ነበር? ለመልሳችሁ ማስረጃ ስጡ::

4/ አንድ ሰው ሌላውን ሰው ከኃጢአት ሊያድነው ይችላል? ለመልሳችሁ ማብራሪያ ስጡ::

5/ ክርስቶስ የተወለደው የት ነበረ?

6/ ክርስቶስ ከሞት ባይነሣ ኖሮ ከኃጢአታችን ሊያድነን ይችል ነበር? ማብራሪያ ስጡ::

7/ የክርስቶስ ወደ ሰማይ ማረግ ለምን አስፈለገ?

8/ ሰው ከኃጢአቱ እንዲድን ምን ማድረግ ያስፈልገዋል?

9/ መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን ባየ ጊዜ:- «እነሆ የእግዚአብሔር በግ» ብሎ ለምን ክርስቶስን እንደ በግ ቆጠረው?

10/ የበግ ደም ሰውን ከኃጢአቱ ሊያድነው የማይችል ከሆነ እግዚአብሔር የእስራኤል ሕዝብ የበግ መሥዋዕት እንዲያቀርቡ ለምን አዘዛቸው?

11/ ዮሐ.3:16ን በቃላችሁ አጥኑ::

## ክፍል ስድስት:- መንፈሳዊ ሕይወት

### ትምህርት 25

**ጥያቄ 58:-** አማኝ በክርስትና ሕይወቱ እንዲያድግ ምን ማድረግ ይገባዋል?
**መልስ:-** አማኝ በክርስትና ሕይወቱ እንዲያድግ መጸለይ÷ የእግዚአብሔርን ቃል መማር÷ ስለ ክርስቶስ መመስከር÷ ከአማኞች ጋር መሰብሰብና ለእግዚአብሔር ፈቃድ መታዘዝ ይገባዋል።

### መንፈሳዊ ዕድገት

ሕፃን ሲወለድ ጸስ ይለናል። ከተወለደ በኋላ ባያድግ ግን ጸስ አይለንም። እንዲያድግ እናቱ በጸንብ ትጠብቀዋለች። እንደዚሁ አንድ ሰው ክርስቶስን ሲቀበል አዲስ እንደተወለደ ሕፃን ሆኖ ማደግ አለበት። አማኝ እንዲያድግ ምን ያስፈልገዋል?

ሀ/ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንዲያድግ የእግዚአብሔር ቃል ያስፈልገዋል፤ 1ጴጥ.2:2።
 1/ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ምግብ ነው። ሕፃን ጥሩ ምግብ ካላገኘ እንደማያድግ እንዲሁም አንድ አማኝ የእግዚአብሔርን ቃል ካልሰማ በመንፈሳዊ ሕይወቱ አያድግም። ኢየሱስ ለሰይጣን:- «ሰው በእግዚአብሔር ቃል እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም» ብሎ መለሰለት፤ ማቴ.4:4። እሑድ እሑድ ወደ ጸሎት ቤት ሄዳችሁ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ። ነገር ግን በሳምንት አንድ ጊዜ ብቻ ምግብ መብላት እንደማይበቃ ሁሉ በሳምንት አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በየቀኑ የእግዚአብሔርን ቃል መስማትና ማጥናት ያስፈልጋል።
 2/ የእግዚአብሔር ቃል ያነጻል፤ ዮሐ.15:3፤ መዝ.118/119/:9-11።
 3/ የጸሎቱን መልስ እንዲያገኝ የእግዚአብሔርን ቃል በልቡ ማኖር ያስፈልገዋል፤ ዮሐ.15:7።
 4/ ለሌሎች መመስከር እንዲችል የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ ያስፈልገዋል።

ለ/ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንዲያድግ ያስፈልገዋል።
 1/ እግዚአብሔር አማኝ የሆነ ሰው ሁሉ እንዲጸልይ አዝዞአል፤ ማቴ.7:7፤ ኤፌ.6:18፤ 1ጢሞ.2:1።
 2/ እግዚአብሔር ከሰው ጋር ለመገናኘት ይፈልጋል፤ ዘፍ.1:26፤ 3:8፤ ያዕ.4:8።
 3/ ከኃጢአቱ ነጻቶ ሰይጣንን እንዲያሸንፍ ጸሎት ያስፈልገዋል፤ 1ዮሐ.1:9፤ ማቴ.26:41።

ሐ/ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንዲያድግ ከሌሎች አማኞች ጋር መተባበር ያስፈልገዋል።
1/ በሐዋርያት ዘመን የነበሩት አማኞች ለመንፈሳዊ አምልኮ ባንድነት ይሰበሰቡ ነበር፤ የሐዋ.2:42።
2/ እግዚአብሔር አማኞችን ለመንፈሳዊ አምልኮ በአንድነት እንዲሰበሰቡ አዘአቸዋል፤ ዕብ.10:25።
3/ የጥምቀት ሥርዓት በሚፈጸምበት ጊዜም ከሌሎች አማኞች ጋር በአንድነት ይሰበሰባሉ፤ የሐዋ.2:41።
4/ የጌታን እራት በሚወስዱበት ጊዜም ከሌሎች አማኞች ጋር በአንድነት ይሰበሰባሉ፤ 1ቆሮ.11:23-26።

መ/ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንዲያድግ ስለ ክርስቶስ መመስከር ያስፈልገዋል።
1/ በሥራውና በአካሄዱ መመስከር ያስፈልገዋል፤ ማቴ.5:14-16።
2/ በአፉ መመስከር ያስፈልገዋል፤ ሮሜ 10:9-10።

ሠ/ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንዲያድግ ራሱን በሙሉ ለእግዚአብሔር መስጠት ያስፈልገዋል፤ ሮሜ 12:1-2። መንፈስ ቅዱስ በእርሱ በኩል ሲሠራ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መፈጸም ይችላል።

## ትምህርት 26

ጥያቄ 59:- አማኝ በቅድስና ሊኖር የሚችለው እንዴት ነው?
መልስ:- አማኝ በቅድስና ሊኖር የሚችለው በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና መሪነት ነው፤ ሮሜ 8:2።

### የመንፈስ ቅዱስ ሥራ

ሀ/ መንፈስ ቅዱስ ሰው ዳግመኛ እንዲወለድ ያደርጋል፤ ዮሐ.3:5።
1/ በመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ የሚወለዱ እነማን ናቸው? ክርስቶስን የተቀበሉ ሁሉ ናቸው።
2/ ዳግመኛ የተወለዱት መቼ ነው? ዳግመኛ የተወለዱት ወዲያው ክርስቶስን በተቀበሉበት ጊዜ ነው።
3/ ዳግመኛ ስለተወለዱ ምን ይሆናሉ?
- የእግዚአብሔር ልጆች ይሆናሉ፤ ዮሐ.1:12።
- አዲስ ፍጥረት ይሆናሉ፤ 2ቆሮ.5:17።

ለ/ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ልብ ውስጥ ይኖራል፤ ዮሐ.14:17፤ 1ቆሮ. 6:19-20።
1/ መንፈስ ቅዱስ ለማን ተሰጠ? ለአማኞች ሁሉ ተሰጠ። መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው የሌላቸው ሰዎች አማኞች አይደሉም፤ ሮሜ 8:9።

2/ መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ልብ ገብቶ መኖር የሚጀምረው መቼ ነው? ክርስቶስን በተቀበለ ጊዜ ነው፤ ገላ.3:2::
3/ መንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ሲኖር ምን ይሠራል?
- ያስተምረል፤ ዮሐ.14:26::
- እውነትን ያስታውቃል፤ ዮሐ.14:17::
- ወደ እውነት ይመረል፤ ዮሐ.16:13::
- ኃጢአትንና የሥጋን ምኞት ለማሸነፍ ያስችላል፤ ሮሜ 8:13፤ ገላ.5:16፤25::
- ክርስቶስ የተናገረውን ያሳስባል፤ ዮሐ.14:26::
- ያጽናናል፤ ዮሐ.14:16፤26::
- በጸሎት ያግዛል፤ ሮሜ 8:26-27::
- አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ስለሆነ ከክፉ ነገር ተለይቶ ለእግዚአብሔር ክብር እንዲኖር ያስችላል፤ 1ቆሮ.6:19-20::

ሐ/ መንፈስ ቅዱስ አማኞችን ለቤዛቸው ቀን ያትማቸዋል፤ ኤፌ.4:30::
1/ በመንፈስ ቅዱስ የታተሙት እነማን ናቸው? በመንፈስ ቅዱስ የታተሙት አማኞች ሁሉ ናቸው::
2/ በመንፈስ ቅዱስ የታተሙት መቼ ነው? በመንፈስ ቅዱስ የታተሙት ክርስቶስን በተቀበሉ ጊዜ ነው፤ ኤፌ.1:13-14::
3/ በመንፈስ ቅዱስ መታተም ምን ይሠራል?
- የማን መሆናቸውን ያሳያል:: ማኅተም ባለ ንብረቱን ያመለክታል::
- ማንም ከእጁ እንዳይነጥቃቸው ይከለክላል::
- የርስታቸው መያዣ ነው፤ ኤፌ.1:13-14::

መ/ መንፈስ ቅዱስ አማኞችን ያጠምቃል፤ 1ቆሮ.12:13::
1/ በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁ እነማን ናቸው? አማኞች ሁሉ ናቸው::
2/ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁት መቼ ነው? አማኞች በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁት ክርስቶስን በተቀበሉ ጊዜ ነው:: ክርስቶስ ወደ ሰማይ ከመሄዱ በፊት ይህንን ተስፋ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጥቶአቸው ነበር፤ የሐዋ.1:4-5:: ይህም በበዓለ ሃምሳ ቀን ተፈጸመ፤ የሐዋ.2:1-3:: በዚህን ቀን መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ሁሉ ላይ ወረደ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰዎች ክርስቶስን ሲቀበሉ ወዲያውኑ በመንፈስ ቅዱስ ይጠመቃሉ::
3/ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ሲጠመቅ ምን ይሆናል?
- የክርስቶስ አካል ይሆናል፤ ኤፌ.1:22-23::
- ክርስቶስ የአካሉ ራስ ነው፥ አማኝ የርሱ አካል ነው፤ 1ቆሮ.12:27::

- ከሌሎች አማኞች ጋር አንድ አካል ይሆናል፤ 1ቆሮ.12:13። ስለዚህ ከሌሎች አማኞች ጋር አንድነት አለው።

ሠ/ መንፈስ ቅዱስ አማኞችን ይሞላል፤ ኤፌ.5:18።
1/ መንፈስ ቅዱስ የሚሞላቸው እነማንን ነው? ልባቸውን በሙሉ ለእግዚአብሔር የሰጡትንና በእምነት የተቀበሉትን ነው። አንዳንድ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ሳይሞሉ ሊቀሩ ይችላሉ።
2/ መንፈስ ቅዱስ አማኞችን የሚሞላቸው መቼ ነው? አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ብዙ ጊዜ ይሞላቸዋል።
3/ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምን ይሠረል? ትምህርት ሃያ ሰባትን ተመልከቱ።

## ትምህርት 27

### የመንፈስ ቅዱስ ሙላት

ሀ/ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ለምን ያስፈልጋል?
1/ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ስለሆነ፤ ኤፌ.5:18።
2/ ለመንፈሳዊ ሥራችን ኃይል እንድንቀበል፤ የሐዋ.1:8።
3/ በቅድስና እንድንኖር፤ ገላ.5:16።
4/ የመንፈስ ፍሬ እንዲታይብን፤ ገላ.5:22-23።

ለ/ የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ልንቀበል የምንችለው እንዴት ነው?
1/ መንፈስ ቅዱስን በመጠማትና በመራብ፤ ማቴ.5:6፤ ዮሐ.7:37-39። በተጠማን ቁጥር ተቀብለን ልንረካ እንችላለን።
2/ ክርስቶስ በሕይወታችን እንዲነግሥ ፈቃደኞች በመሆን:-
- ኃጢአታችንን መናዘዝ ያስፈልጋል፤ 1ዮሐ.1:9።
- ኃጢአታችንን መተው ያስፈልጋል፤ ምሳሌ 28:13። ኃጢአታችንን ለመተው ባንወድ እንኳን፥ እንድንተወው ኃይል እንዲሰጠን እግዚአብሔርን እንለምን። ኃጢአታችንን ለመተው ወስነን መቅረብ አለብን። አባካኙ ልጅ አሳቡን ቆርጦ ተነሥቶ ወደ አባቱ በመጣ ጊዜ አባቱ በደስታ ተቀበለው፤ ሉቃ.15። ሳናውቅ የሠረነውን ኃጢአት እግዚአብሔር እንዲያሳየንና እንዲያነጻን እንለምነው፤ መዝ.138/139/:23-24፤ መዝ.50/51/:7፤10። ልባችንን በሙሉ ለእግዚአብሔር ሰጥተን ለመታዘዝ ፈቃደኞች መሆን ያስፈልገናል። እርሱ ጌታችን ነው፤ ሮሜ 6:13፤ 12:1።

፫/ በእምነት ሙላቱን መቀበል ያስፈልገናል። ክርስቶስ በልባችን ውስጥ ሙሉ ሥልጣን እንዲኖረው ከፈቀድን እርሱ በጸጋ እንደሚሞላን እንመን። ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት ብዙ ሰዓት መቆየትና መለመን፥ ሌላ ሰው መጥቶ እጁን እስኪጭንብን ድረስ ማልቀስና መጨነቅ አስፈላጊ አይደለም። በእምነትክርስቶስን እንደተቀበልን እንዲሁ በእምነት የመንፈስ ቅዱስን ሙላት እንቀበላለን።

ሐ/ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምልክቶች ምንድር ናቸው?

፩/ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ይታያል፤ ገላ.5:22-23። በልዩ ቋንቋ መናገርና ሌላ ሥጦታ መቀበል የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምልክቶች አይደሉም። ሁለተኛ ስንወለድ መንፈስ ቅዱስ እንደፈለገ ልዩ ልዩ ስጦታ ይሰጠናል፤ 1ቆር. 12:11። የቆሮንቶስ ሰዎች ብዙ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ነበሯቸው። ነገር ግን ብዙ ኃጢአት ይሠሩ ነበር። በመንፈስ ቅዱስ አልተሞሉም ነበር። በመንፈስ ስንመላለስግን ለኃጢአት አንገዛም፤ ገላ.5:16።

፪/ ለሥራችን ኃይል እንቀበላለን። ጸቀ መዘሙርት በመንፈስ ቅዱስ በተሞሉ ጊዜ በድፍረት የእግዚአብሔርን ቃል ተናገሩ፤ የሐዋ.4:8። አማኞች ከሆናችሁ በመንፈስ ቅዱስ አዲስ ልደት አገኝታችኋል፥ ታትማችኋል፤ በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቃችኋል፥ መንፈስ ቅዱስ በልባችሁ አለ። ይህን ሁሉ እግዚአብሔር በእናንተ የሚሠረው ኢየሱስን በእምነት ስትቀበሉ ነው። «መንፈስ ይሙላባችሁ» የሚል ቃስ ለኛ የተሰጠ ትእዛዝ ነው። ስለዚህ በመንፈስ መሞላት የኛ ኃላፊነት ነው። ሙላት ሊጎድልብን ይችላል። እንደገና ልንሞላ እንችላለን፤ የሐዋ.2:4፤ 4:8፤31። እግዚአብሔር የሚፈልገው መንፈስ ቅዱስ ሁልጊዜ እንዲሞላን ነው። እርሱ ሊሞላን ስለሚፈልግ በእምነት ወደ እግዚአብሔር ቀርበን ሙላቱን መቀበል የኛ ፋንታ ነው።

## ትምህርት 28

**ጥያቄ 60:-** መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ሕይወት ውስጥ አድሮ ምን ይሠረል?
**መልስ :-** መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ሕይወት ውስጥ አድሮ የመንፈስን ፍሬ ያፈረል፤ ገላ.5:22-23።

### የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ

ሀ/ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ አስፈላጊነት:-

1/ ሰው ከዳነ በኋላ በዚህ ዓለም የሚቆየው ለእግዚአብሔር ፍሬ እንዲያፈረ ነው። እግዚአብሔር የማያፈረውን ቅርንጫፍ ያስወግደዋል፤ ዮሐ.15:2።

2/ ፍሬ የሚያፈረው ለእግዚአብሔር ክብር ነው፤ ዮሐ.15:8።
3/ ዛፍ በሚያፈረው ፍሬ እንደሚታወቅ ሁሉ ሰዎች በሥራቸው ይታወቃሉ፤ ማቴ.7:16። የመንፈስ ፍሬ እንጂ የሥጋ ፍሬ በአማኞች ውስጥ መታየት የለበትም፤ ያዕ.3:9-10።

ለ/ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ እንዴት ይገኛል?
1/ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሚገኘው መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ልብ ውስጥ ሞልቶ ሲገዛቸው ነው፤ ኤፌ.5:18።
2/ የስንዴ ቅንጣት በመሬት ወድቃ ሞታ ብዙ ፍሬ እንደ ምታፈረ፥ እንዲሁ አማኝ ለራሱ አሳብና ምኞት ቢሞት ብዙ ፍሬ ሊያፈራ ይችላል፤ ገላ.5:24፤ ዮሐ.12:24።
3/ ቅርንጫፍ ከግንዱ ሲለይ ፍሬ ማፍረት እንደማይችል እንዲሁም አማኝ ከክርስቶስ ቢለይ በራሱ ኃይል ፍሬ ማፍረት አይችልም፤ ዮሐ.15:4። ፍሬ የሚገኘው ቅርንጫፍ ብቻውን በመሥራቱ ሳይሆን ከግንዱ ጋር አብሮ በመኖሩ ነው። አማኝ ፍሬ የሚያፈረው በክርስቶስ ውስጥ ኖሮ ክርስቶስ በእርሱ በኩል ሲሠራ ነው፤ ዮሐ.15:5።
4/ ፍሬ የሚያፈረውን ሁሉ አብዝቶ እንዲያፈረ ገበሬው እንደሚያበጃጀው መንፈስ ቅዱስም አማኙን ስለኃጢአቱ በመውቀስ ለእግዚአብሔር ክብር የማይሆነውን ነገር ከእርሱ ያስወግዳል፤ ዮሐ.15:2።

ሐ/ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ዓይነቶች፥ ገላ.5:22-23።
1/ ፍቅር:- 1ቆሮ.13:4-7። ይህ ፍቅር ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኝ እንጂ ሰው በተፈጥሮ ባሕርዩ የሚያገኘው አይደለም። ሰው ሌላ ነገር ሁሉ ቢኖረው ፍቅር ግን ከሌለው ምንም አይጠቅመውም፤ 1ቆሮ.13:1-3።
2/ ደስታ:- ይህ ደስታ ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኝ እንጂ በዓለም አስደሳች ከተባሉት ነገሮች የሚገኝ አይደለም። ይህ ደስታ ሰው አሳዛኝ ነገር በሚያጋጥመው ጊዜ እንኳ ከልቡ ውስጥ ሊጠፋ የማይችል ደስታ ነው፤ ፊልጵ.4:4።
3/ ሰላም:- በችግርና በሁከት ጊዜ እንኳ ከአማኙ አይርቅም፤ ፊልጵ.4:7።
4/ ትዕግሥት:- ሰዎች አማኙን በሚያስቸግሩት፥ በሚያሳድዱትና በሚሰድቡት ጊዜ በትዕግሥት መቀበል የሚያስችለው ነገር ነው።
5/ ቸርነት:- በለጋስነት መስጠት ወይም መርዳት ነው።
6/ በጎነት:- ክፋትን በመጥላት በአሳብና በሥራ ፍጹም እውነተኛ መሆን ነው።
7/ እምነት:- በቃልና በሥራ ታማኝ መሆን ነው።
8/ የውሃት:- በቶሎ አለመቆጣት፥ ራስን ከፍ ባለማድረግ እና በትሕትና

የሰውን ምክር መስማትና እንዲሁም ደግሞ ሌሎችን በትሕትና መምከር ነው፤ 2ጢሞ.2:24-25::

9/ ራስን መግዛት:- በድርጊትና በአሳብ የራስን ፍላጎት ትቶ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ራስን መቆጣጠርና በመጠን መኖር ነው:: ይህ ፍሬ በሙሉ በክርስቶስ ሕይወት ውስጥ እንደታየ በአማኞች ሕይወት ውስጥ ደግሞ መታየት አለበት::

## የክፍል ስድስት ጥያቄዎች

1/ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንዲያድግ የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?

2/ እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ ስለሚገኝ አንድ ሰው ወደ ጸሎት ቤት በመሄድ ፋንታ በራሱ ቤት ቃሉን አንብቦ መጸለይ በቂው ነው?

3/ መንፈስ ቅዱስ ወደ ሰው ልብ ገብቶ የሚኖረው መቼ ነው?

4/ በመንፈስ ቅዱስ መታተም ማለት ምን ማለት ነው?

5/ 1ቆሮ.12:13 ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አገልግሎት ምን ያስተምራል?

6/ አማኞች ሁሉ ከመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ ይወለዳሉ? አማኞች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ይሞላሉ?

7/ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ምንድነው?

8/ 1ቆሮ.6:19-20 ምን ያስተምራል?

9/ ኤፌ.5:18ን በቃላችሁ አጥኑ::

## ክፍል ሰባት:- ቤተ ክርስቲያን

### ትምህርት 29

**ጥያቄ 61:- ቤተ ክርስቲያን ምንድናት?**

**መልስ :-** ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ሳትሆን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነጽተው አንድ አካል የሆኑት የአማኞች ኅብረት ናት::

### ቤተ ክርስቲያን

ሀ/ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል የሚናገረው ስለ አማኞች እንጂ ስለ ሕንጻው አይደለም:: ይህንንም ከሚቀጥሉት ጥቅሶች ለመረዳት እንችላለን::

1/ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ወደደ፤ ኤፌ. 5:25:: ክርስቶስ የወደደው ሰውን እንጂ ሕንጻውን አይደለም::

2/ ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያን ሰላምታ ይልክ ነበር፤ ሰላምታ መቀበል የሚችለው ሰው እንጂ ሕንጻ አይደለም:: እውነተኛይቱ ቤተ

የአማኞች መመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። አማኞች በመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያ ሥራቸውን ከፈጸሙ እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን እንደሚሰጣቸው ተስፋ ሰጥቶአል፤ 2ቆሮ.9፡8። ማንም የቤተ ክርስቲያን አባል ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ ማስተማር አይገባውም። በስም ብቻ የቤተ ክርስቲያን አባሎች ናችሁ? ምናልባት ተጠምቃችኋል፤ የጌታን እራት ትወስዳላችሁ፤ ወደ ስብሰባም ትመጣላችሁ፤ ነገር ግን ዳግመኛ ካልተወለዳችሁ ስማችሁ በሕይወት መጽሐፍ አልተጻፈም። በመጨረሻ ቀን እንደ እንክርዳድ ወደ እሳት እንዳትጣሉ ራሳችሁን መርምሩ፤ ማቴ.13፡30፤ ራእይ 20፡15።

## ትምህርት 30

ጥያቄ 62:- የቤተ ክርስቲያን ራስ ማን ነው?
መልስ :- የቤተ ክርስቲያን ራስ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ ኤፌ.5፡23።

### ክርስቶስና ቤተ ክርስቲያን

ሀ/ በክርስቶስና ቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን ግንኙነት የሚገልጹ አራት ምሳሌዎች:-

1/ ክርስቶስና ቤተ ክርስቲያን በአካል ራስና በአካል ክፍሎች ተመስለዋል። ክርስቶስ የአካሉ ራስ ሲሆን አማኞች ደግሞ በሌሎች የአካል ክፍሎች ተመስለዋል፤ ኤፌ.1፡22-23። የአካልክፍሎች ለራስ አለመታዘዝ ሕመም እንደሆነ ሁሉ የአካል ክፍሎች የሆኑት ምእመናን የአካል ራስ ለሆነው ለክርስቶስ አለመታዘዝ የቤተ ክርስቲያን ጽካም ነው። አካላችንን ለእግዚአብሔር ስናቀርብ የርሱን ሥራ እንጂ ኃጢአት አንሥራም፤ ሮሜ 6፡13፤ 12፡7።

2/ ክርስቶስና ቤተ ክርስቲያን በሙሽራ ተመስለዋል። ክርስቶስ ሙሽራው ሲሆን ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የክርስቶስ ሙሽራ ናት፤ ራእይ 21፡2። ክርስቶስ ሙሽራይቱን ስለወደዳት ሕይወቱን ለርስዋ አሳልፎ ሰጠ። እኛም ደግሞ እርሱን መውደድ፥ ማክበርና መታዘዝ አለብን፤ ኤፌ.5፡25-32።

3/ ክርስቶስና ቤተ ክርስቲያን በወይን ግንድና በቅርንጫፍ ተመስለዋል። ክርስቶስ የወይን ግንድ ሲሆን አማኞች ደግሞ ቅርንጫፎች ናቸው፤ ዮሐ.15፡5። ቅርንጫፎች ብቻቸውን ፍሬ ማፍረት እንደማይችሉ ሁሉ አማኞችም በክርስቶስ ውስጥ ካልኖሩ ፍሬ ማፍረት አይችሉም፤ ፍሬ የማያፈራ ቅርንጫፍ ይወገዳል፤ ዮሐ.15፡4።

4/ ክርስቶስና ቤተ ክርስቲያን በእረኛና በበጎች ተመስለዋል። እረኛው ክርስቶስ ሲሆን በጎቹ ደግሞ አማኞች ናቸው፤ ዮሐ.10:11፤ ዕብ.13:20። እረኛ በጎቹን እንደሚጠብቅ ክርስቶስም አማኞችን ይጠብቃል። በጎች የእረኛውን ድምጽ አውቀው እንደሚከተሉት አማኞች ደግሞ ክርስቶስን አውቀው ይከተላሉ።

ለ/ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ይወዳል።

1/ ስለ ወደዳት ሞቶላታል፤ ኤፌ.5:25-26። ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ።

2/ ቤተ ክርስቲያን ንጹሕና ቅድስት እንድትሆን ይፈልጋል፤ ኤፌ.5:27።

3/ ክርስቶስ በስሙ ከሚሰበሰቡት ጋር እንደሚሆን ቃል ገብቶአል፤ ማቴ.18:20።

4/ በአብና በወልድ መካከል ያለው አንድነት በአማኞችም ዘንድ ደግሞ እንዲኖር ክርስቶስ ጸለየ፤ ዮሐ.17:11፤ 22-23። የአንድነቱ መሠረት እግዚአብሔር ነው። በዚህም መሠረት አማኞች እርስ በርሳቸው አንድነት ሊኖራቸው ይገባል።

5/ እግዚአብሔር አማኞችን ከክፉ እንዲጠብቃቸው ክርስቶስ ጸለየ፤ ዮሐ.17:15።

## ትምህርት 31

### የቤተ ክርስቲያን ተግባር

ሀ/ ኅብረት:-

1/ አማኞች እግዚአብሔርን ለማምለክ ለማመስገንና ለመጸለይ ከሌሎች አማኞች ጋር ይገናኛሉ። ክርስቲያኖች በእምነታቸው ጠንክረው እንዲሆኑ ከሌሎች አማኞች ጋር አንድነት እንዲኖራቸው አስፈላጊ መሆኑን እግዚአብሔር ስላወቀ የክርስቲያኖች መሰብሰብ እንዳይቋረጥ ተናግሮአል። የሐዋ.2:42፤ ዕብ.10:25። አማኞች እርስ በርሳቸው መፋቀር፥ መተሳሰብ፥ መጽናናትና መተባበር ያስፈልጋቸዋል።

2/ አማኞች ከሌሎች ጋር ሲሆኑ የእግዚአብሔርን ቃል ይማራሉ። አንድ ሰው ገና ሲያምን በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሕፃንን ይመስላል። ለሕፃን በመጀመሪያ ወተት በኋላም ትንሽ ጠንከር ያለ ምግብ ያስፈልገዋል። እግዚአብሔር አማኞች በእምነታቸው ጠንክረው ክርስቶስን ወደ መምሰል እንዲያድጉ የሚረዱአቸውን አስተማሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አድርጎአል፤ 1ቆሮ.12:28።

የእግዚአብሔርን ቃል ያስተምራሉ፤ የታመሙትን ጠይቀው ይጸልዩላቸዋል፤ ያዕ.5:14፤ አማኞችን ያጽናናሉ፤ ይገሥጻሉ፤ ይመክራሉ::

3/ ዲያቆናት:- የዲያቆናት ተግባር ከሽማግሌዎች ተግባር የተለየ ነው:: ዲያቆናት የሚመረጡት የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችና መጋቢ መንፈሳዊ የሆነውን ሥራቸውን ለመሥራት በቂ ጊዜ እንዲያገኙ እንዲረዷቸው ነው:: ለመጀመሪያዎቹ ዲያቆናት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተሰጠው የሥራ ምድብ በሐዋ.6:2-6 ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ይኸውም ገንዘብና ምግብ ለድሆችና ለመበለቶች ማከፋፈልና በጠቅላላውም ቤተ ክርስቲያንን ማገልገል ነበር::

4/ ሌሎች አገልጋዮች:- በእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን የሚረዱ እረኞች ወይም መጋቢዎች፥ መምህራንና ወንጌላውያን ሊገኙ ይችላሉ፤ ኤፌ.4:11-13::

ሐ/ የአባሎች ሥራ:-

1/ እያንዳንዱ አማኝ ካህን ነው፤ ራእይ 1:6:: በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር በጸሎት መቅረብ ይችላል፤ ዕብ.4:16:: ካህን ሰዎችን በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ፊት የሚያቀርብ ሰው ነው፤ እግዚአብሔርም በእርሱ አማካይነት ለሰዎች ይናገራል::

2/ አማኝ የእግዚአብሔር መልእክተኛ በመሆን «ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ» እያለ የእግዚአብሔርን ቃል ያስተምራል፤ 2ቆሮ.5:20:: ሐዋርያት በኢየሩሳሌም ሲቆዩ የቀሩት አማኞች ቃሉን እያስተማሩ ዞሩ፤ የሐዋ.8:4::

3/ እግዚአብሔር እያንዳንዱ አማኝ የተለያዩ ሥራዎችን እንዲሠራ ስጦታን ይሰጠዋል፤ 1ቆሮ. 12:6:: እያንዳንዱ አማኝ እግዚአብሔር በሰጠው ስጦታ ተጠቅሞ ሲሠራ ቤተ ክርስቲያን እያደገች ትሄዳለች::

4/ እያንዳንዱ አማኝ ሳያቋርጥ ወደ ጸሎት ቤት መሄድ አለበት::

5/ እያንዳንዱ አማኝ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ገንዘብ መስጠት አለበት፤ 2ቆሮ.9:7፤ 1ቆሮ.16:2::

6/ እያንዳንዱ አማኝ ሥራውን በትክክል በመሥራት ጥሩ ምስክርነት ሊሰጥና ሌሎችንም ወደ ክርስቶስ ሊመራ ይችላል፤ ሮሜ 12:14-21:: ክርስቶስ እንዳገለገለ እንዲሁ አማኞችም ለራሳቸው ክብርን ሳይፈልጉ ማገልገል አለባቸው፤ ማር.10:44-45:: ነገር ግን አማኞች የሚያገለግሏቸውን ሰዎች በሚገባ ማክበር አለባቸው፤ 1ጢሞ.5:17::

## የሽማግሌዎችና የዲያቆናት ምርጫ

ሀ/ ኤጲስ ቆጶስ ወይም ሽማግሌ ማሟላት የሚገባው ግዴታዎች፤
1ጢሞ.3፡2-7።
በግል ሕይወቱ፡-

1/ አገልጋይ መሆን እንጂ ሹመትንና ክብርን መፈለግ የለበትም፤ ማር.10፡44-45።
2/ የማይነቀፍ፡- ስሕተት የሌለበት ፍጹም ሰው ስለማይገኝ ፍጹም ይሁን ባይባልም ትክክለኛ ሰው መሆን አለበት።
3/ የአንዲት ሚስት ባል፡- ሚስት ማግባት ተፈቅዶአል፤ ነገር ግን አንድ ብቻ ያገባ መሆን አለበት።
4/ ልከኛ፡- ሰይጣን እንዳያስተው ለራሱ ሕይወት የሚጠነቀቅና አባሎቹን በትጋት የሚጠብቅ ለመንጋውም የሚገባውን ሁሉ የሚያደርግ መሆን አለበት፤ 1ጴጥ.5፡8።
5/ ራሱን የሚገዛ፡- በሚያደርገውና በሚያስበው ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ እንዳይሄድ ራሱን መቆጣጠር የሚችል መሆን አለበት፤ የራሱን መንፈስ የሚገዛ ሰው አንዲት ከተማን ከሚገዛ ሰው ይበልጣል፤ ምሳ.16፡32። ራስን መግዛት የመንፈስ ፍሬ ነው፤ ገላ.5፡23።
6/ እንደሚገባው የሚሠራ፡- መሥራት የሚገባውን ሁሉ ባለመታከት የሚሠራና ከክፋ ሥራ ሁሉ የሚርቅ መሆን አለበት።
7/ እንግዳ ተቀባይ፡- ለራሱ ብቻ የማያከማች ነገር ግን ስለሌሎች የሚያስብ፥ የተሰደዱትን የሚያስተናግድ፥ የተቸገሩትን የሚረዳ መሆን አለበት። የጥንት ሽማግሌዎች ራሳቸውንና ሌሎችን የሚረዱ እንጂ ለእርዳታ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመለከቱ አልነበሩም።
8/ ለማስተማር የሚበቃ፡- የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት አውቆ ለሌሎች ማካፈል የሚችል መሆን አለበት።
9/ የማይሰክር፡- አንድ ብርጭቆ መጠጣት ሁለተኛ ወደ መጐምና ወደ ስካር ስለሚመራ የሚያሰክር መጠጥ በፍጹም የማይጠጣ መሆን አለበት። ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ካህናት ናቸው፤ ራእይ1፡5-6፤ 1ጴጥ.2፡5። እግዚአብሔር ካህናቱን ወይን እንዳይጠጡ አዘዛቸው፤ ዘሌዋ.10፡9፤ኤፌ.5፡18። የአማኞች አካላት የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ናቸው፤ 1ቆሮ.6፡19-24።
10/ የማይጨቃጨቅ ነገር ግን ገር የሆነ፡- በፍቅር የሚኖር መሆን አለበት።
11/ የማይከራከር፡- ትዕግሥተኛ መሆን አለበት።

12/ ገንዘብን የማይወድ:- በገንዘብ ፍቅር ያልተጠመደና የሌሎችን ሀብት የማይመኝ መሆን አለበት።

በቤተሰቡ መካከል:-

13/ ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም በማስተዳደር ጥሩ ምሳሌ መሆን አለበት። የራሱን ቤት በጸምብ ሊያስተዳድር የማይችል ከሆነ ቤተ ክርስቲያንን እንዴት ሊጠብቅ ይችላል? ልጆቹ እና ሚስቱ ጥሩ ምሳሌዎች ካልሆኑ የሽማግሌው ምስክርነት ይበላሻል።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ:-

14/ በትዕቢት ተነፍቶ በዲያብሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ አዲስ ክርስቲያን አይሁን። በእግዚአብሔር ቃል ላይ በሚገባ ካልተመሠረተ በራሱ ዕውቀት ለመመረት ይሞክር ይሆናል። ዲያብሎስ በትዕቢት ምክንያት ወድቋል። አዲስ ክርስቲያን ስልጣን ሲያገኝ በትዕቢት ሊሞላ ይችላል።

በአካባቢው:-

15/ በውጭ ካሉት ሰዎች መልካም ምስክር ሊኖረው ይገባል። ብዙውን ጊዜ ያላመኑት ሰዎች ክርስቶስን የማይቀበሉበት ምክንያት በክርስቲያን መሪዎች ሕይወት ውስጥ የማያስደስት ነገር በማግኘታቸው ነው።

ለ/ ዲያቆናት ማሟላት ያለባቸው ግዴታዎች፤ 1ጢሞ.3:8-12።

1/ በመልካም የተመሰከረላቸው፤ የሐዋ.6:3።

2/ መንፈስ ቅዱስ የሞላባቸው፤ የሐዋ.6:3።

3/ ጥበብ የሞላባቸው፤ የሐዋ.6:3።

## ትምህርት 34

## አሥራትና ምጽዋት

ሀ/ በብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች ለእግዚአብሔር ይሰጧቸው የነበሩት የስጦታ ዓይነቶች:-

1/ በኩረት:- የእስራኤል ሰዎች ከግብፅ አገር ሊወጡ ሲሉ እግዚአብሔር የግብፅ ሰዎችን የበኩር ልጆችና ከብቶች ገደለ፤ ዘፀ.12:29። እስራኤላውያን የበኩር ልጆቻቸው እንዳይሞቱ ጠቦት አርደው ደሙን በበር ላይ ረጭተው ነበር። ከዚያ በኋላ ለመታሰቢያ ከሰውና ከእንስሳ ሁሉ የተወለደውን በኩር ወንድ ለእግዚአብሔር ይሰጡ ነበር፤ ዘፀ.13:1።

2/ አሥረት:- እግዚአብሔር ለእርሱ ሥረና ለሠረተኞቹ÷ ሰዎች ከአሥር እጅ አንድ እንዲሰጡ አዘአቸው ነበር፤ ዘኁ.18:26፤ ዘሌዋ.27:32።  ሰዎች ባይሰጡ ከእግዚአብሔር እንደሰረቁ ተቆጥረው የተረገሙ ይሆኑ ነበር፤ ሚል.3:8-9። እግዚአብሔር አሥረት የሰጡትን ሰዎች ከመጠን በላይ ይባርካቸው ነበር፤ሚል.3:10።

3/ ሰዎች በገዛ ፈቃዳቸው ይሰጡት የነበረው ስጦታ÷ ዕዝረ 1:6፤ 2:68።  ይህም ከበኩረትና ከአሥረት በላይ ሌላ ተጨማሪ ስጦታ ነበረ፤ ዘፀ.25:1-2፤35:21-22፤ 36:3-7።

ለ/ በአዲስ ኪዳን ዘመን በሕግ ሳይሆን በውድ ለእግዚአብሔር እንሰጣለን።

1/ የእግዚአብሔር አንዲያ ልጁን ለእኛ መስጠት እኛ ምን ያህል ለእርሱ ልንሰጠው የሚያስፈልገን የመሆኑ ምሳሌ ነው፤ ዮሐ.3:16፤ 2ቆሮ.9:15።

2/ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብሩን ባለጸጋነቱንም ትቶ ወደዚህ ዓለም ወርዶ ሕይወቱን ስለእኛ አሳልፎ ሰጠ፤ 2ቆሮ.8:9፤ ፊልጵ.2:7-9።

3/ አስቀድመን ራሳችንን መስጠት ያስፈልገናል፤ 2ቆሮ.8:5፤ ሮሜ 12:1።  ራሳችንን ከሰጠን በኋላ ከገንዘባችን መስጠት ከባድ አይሆንም።

4/ ሰዎች በሕግ ከአሥር አንድ ከሰጡ÷ በአሁኑ ዘመን የእግዚአብሔርንና የክርስቶስን ስጦታ ስናስብ ከፍቅራችን የተነሣ ከአንድ አሥረኛ በላይ ለመስጠት ፈቃደኞች አንሆንም?

ሐ/ እንዴት እንስጥ?

1/ በሐዘን ወይም በግድ ሳይሆን በደስታ እንስጥ፤ 2ቆሮ.9:7።
2/ እያንዳንዳችን በልባችን እንዳሰብን እንስጥ፤ 2ቆሮ.9:7።
3/ እግዚአብሔር እንዳሰጠን መጠን እንስጥ፤ 1ቆሮ.16:1-2፤ 2ቆሮ.8:12።
4/ ሳንነፍግ በልጋስነት እንስጥ፤ 2ቆሮ.8:1-4፤ ሮሜ 12:8።
5/ ለሰዎች ታይታ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ብለን እንስጥ፤ ማቴ.6:1። ሰዎች እንዲያዩን ብንሰጥ ከእግዚአብሔር ምንም አንቀበልም።
6/ ከሳምንቱ በመጀመሪያ ቀን÷ ማለትም እሑድ እንስጥ፤ 1ቆሮ.16:1-2።
7/ ሌሎችን እያዋረድን በስጦታችን እንድንመካ ሳይሆን እግዚአብሔርን ስለወደድን የሚቻለንን እንስጥ፤ሉቃስ 18:9-14፤ ማር.12:41-44።

መ/ ስለ መስጠት እግዚአብሔር የሰጣቸው ማስጠንቀቅያዎችና ተስፋዎች:-

1/ ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነው፤ 1ጢሞ.6:10።

2/ ገንዘባችን ሊጠፋብን ከሚችልበት ቦታ ከማከማቸት ይልቅ ሊጠፋብን ከማይችልበት ቦታ እናድርግ፤ ማቴ.6:19-21።
3/ እግዚአብሔር እንደሚፈልግ ብናደርግ የሚያስፈልገንን ይሰጠናል፤ ማቴ.6:33።
4/ ለእግዚአብሔር ብንሰጥ ይባርከናል፤ ሚል.3:10፤ ፊልጵ.4:16-19፤ ምሳሌ 19:17።
5/ እኛ በምንሰጠው መጠን እግዚአብሔር ይሰጠናል፤ ሉቃስ 6:38፤ 2ቆሮ.9:6-11።
6/ ለእግዚአብሔር ብለን ስንሰጥ እግዚአብሔር ይከበረል፤ 2ቆሮ.9:12-14።
7/ ስለ ስጦታችን ማንም እንዳይነቀፈን ለታማኝ ሰዎች መስጠት ያስፈልገናል፤ 2ቆሮ.8:18-21። እነርሱም:- «የእግዚአብሔር ገንዘብ ነው» ብለው በጸንብ መጠበቅና ለእግዚአብሔር ሥራ በታማኝነት ማዋል ይኖርባቸዋል።

## የክፍል ሰባት ጥያቄዎች

1/ ቤተ ክርስቲያን ምንድር ናት? ለመልሳችሁ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ ጥቀሱ።
2/ ሰዎች የቤተ ክርስቲያን አባሎች እንዲሆኑ ማሟላት የሚገባቸው ነጥቦች ምንድር ናቸው?
3/ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን ግንኙነት የሚገልጹ ሶስት ምሳሌዎችን ጻፉ።
4/ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ስለወደዳት ምን አደረገላት?
5/ ላላመኑት ሰዎች የቤተ ክርስቲያን ተግባር ምንድነው?
6/ ማቴ.18:15-17 ምን ያስተምረል?
7/ ቤተ ክርስቲያን አባሎችዋን በልዩ ልዩ ምክንያት መገሰጽ ያስፈልጋታል። ከሚቀጥሉት ጥቅሶች በምንና በምን ምክንያት መገሰጽ እንዳለባት ጻፉ። ቲቶ 1:13
1ጢሞ.5:20
1ቆሮ.5:1-5።
8/ ሀ. ቤተ ክርስቲያን ምን ዓይነት ቅጣት ልትሰጥ ትችላለች? 1ቆሮ.5:5፤13።
ለ. የቅጣቱ ዓላማ ምንድነው?
ሐ. ቤተ ክርስቲያን ስትቀጣ እንዴት አድርጓ መቅጣት አለባት?
1ቆሮ.10:12
ማቴ.7:3-5
1ቆሮ.13:4።
9/ የቤተ ክርስቲያን አባሎች ተግባሮች ምንድር ናቸው?
10/ የሽማግሌዎች ሥራዎች ምንድናቸው?

11/ ለቤተ ክርስቲያን ሽማግሌነት ምርጫ የሚቀርቡ ሰዎች ማሟላት የሚገባቸውን ስምንት ነገሮች ጻፉ::
12/ ዲያቆናት ማሟላት የሚገባቸው ግዴታዎች በ1ጢሞ.3:8-12 ይገኛሉ:: የዲያቆናትን ግዴታዎች ከሽማግሌዎች ግዴታዎች ጋር አነጻጽሩ::
13/ ኤፌ.5:27ን በቃላችሁ አጥኑ::

## ክፍል ስምንት:- የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች

### ትምህርት 35

ጥያቄ 64:- ቅዱስና ልዩ ትኩረት የተሰጣቸው ሁለቱ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች ምንና ምን ናቸው?

መልስ:- ቅዱስና ልዩ ትኩረት የተሰጣቸው ሁለቱ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች ጥምቀትና የጌታ እራት ናቸው::

### ጥምቀት (1)

ሀ/ የዮሐንስ ጥምቀት:-

1/ የዮሐንስ ጥምቀት ከክርስቶስ ሞት በፊት የነበረ ሲሆን ሕዝቡን ከኃጢአት ሊያድን መድኃኒት እንደሚመጣ የሚያመለክት ምሳሌ ነበረ::

2/ የዮሐንስ ጥምቀት የንስሐ ጥምቀት ነበር፤ ሰዎች ስለ ኃጢአታቸው መጸጸታቸውን ለማሳየት በዮሐንስ ይጠመቁ ነበር::

3/ ይሁን እንጂ የዮሐንስ ጥምቀት ሰዎች በአዲስ ሕይወት እንዲኖሩ ኃይል ሊሰጣቸው አልቻለም:: የዮሐንስ ጥምቀት ክርስቶስ መጥቶ ሰዎችን በመንፈስ ቅዱስ እንደሚያጠምቅ ያመለክት ነበር:: ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ሲያጠምቅ አዲስ ሕይወት ይገኛል:: አሁን ክርስቶስን የተቀበሉ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ይጠመቃሉ፤ ዮሐ.1:29-34::

ለ/ የክርስቶስ ጥምቀት :-

1/ ክርስቶስ በሠላሣ ዓመቱ ተጠመቀ::

2/ የተጠመቀው በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ ሲሆን ያጠመቀው ዮሐንስ ነበር፤ ማቴ.3:13-17::

ሐ/ ክርስቶስ ለምን ተጠመቀ?

1/ ክርስቶስ የተጠመቀው ኃጢአትን ለመናዘዝ አልነበረም::

2/ ክርስቶስ የተጠመቀው የእግዚአብሔርን ፈቃድና ጽድቅን ሁሉ ለመፈጸም ነበር፤ ማቴ.3:15:: እግዚአብሔር ዮሐንስ ሰዎችን እንዲያጠምቅ ልኮት ነበር:: ኢየሱስ ለዮሐንስ ጥምቀት ታዛዥ ሆነ::

3/ ክርስቶስ የተጠመቀው ከአማኞች ጋር ያለውን አንድነት ለማሳየትና የጸጎነነታችን ሬስ መሆኑን ለመግለጽ ነበር።
4/ ክርስቶስ የተጠመቀው ለእግዚአብሔር ሥራ በፍጹም የተሰጠ መሆኑንና ወደፊት በመስቀል ላይ በመከራ እንደሚጠመቅ ለማሳየት ነበር።
5/ ክርስቶስ የተጠመቀው የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ለማረጋገጥ ነበር፤ ማቴ.3:17። ኢየሱስ ክርስቶስ ሲጠመቅ መንፈስ ቅዱስ እንደሚወርድበትና በዚህም ክርስቶስ መሆኑ እንደሚታወቅ ለዮሐንስ ምልክት ተሰጥቶት ነበር፤ ዮሐ.1:33።

መ/ አሁን አማኝ ለምን ይጠመቃል?
1/ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለመፈጸም ይጠመቃል፤ ማቴ.28:19፤ ማር.16:15-16።
2/ ከክርስቶስ ጋር ተባባሪና ከሌሎች አማኞች ጋር አንድ መሆኑን በሕዝብ ፊት ለመመስከር ይጠመቃል፤ የሐዋ.2:41-42።
3/ የክርስቶስን ምሳሌ ለመከተል ይጠመቃል፤ 1ጴጥ.2:21።

ሠ/ የጥምቀት ትርጉሙ ምንድነው?
1/ ጥምቀት ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆኑንና የራሱን አሳብና ፈቃድ እርግፍ አድርጎ በመተው በክርስቶስ አሳብና ፈቃድ ለመኖር በሰው ፊት መወሰኑን የሚያረጋግጥ ምልክት ነው፤ ሮሜ 6:3።
2/ በጥምቀት ውኃ ውስጥ መግባት ከክርስቶስ ጋር መሞትን፥ ወደ ውስጥ መጥለቅ ከክርስቶስ ጋር መቀበርን፥ እንዲሁም ከውኃ ውስጥ መውጣት ከክርስቶስ ጋር በአዲስ ሕይወት ለመኖር መነሣትን መመስከር ነው። ስለዚህ አንድ ክርስቲያን ሲጠመቅ ኃጢአት እንዳይገዛው ከክርስቶስ ጋር መሞቱንና በአዲስ ሕይወት ለመኖር መነሣቱን ይመሰክራል፤ ሮሜ 6:4-8።
3/ ጥምቀት አማኞች ሁሉ በአንድ መንፈስ አንድ አካል መሆናቸውን የሚያረጋግጥ መግለጫ ነው፤ 1ቆር. 12:13። ውጫዊው ለሰው የሚታየው የውኃ ጥምቀት ሥርዓት በውስጥ የተደረገውንና የማይታየውን የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ስለሚያሳይ ሰው ሲጠመቅ ከሌሎች አማኞች ጋር አንድ አካል ወይም አንድ ቤተሰብ መሆኑን ያመለክታል።

## ትምህርት 36

ጥያቄ 65:- ጥምቀት ምንድነው?
መልስ:- ጥምቀት አማኝ ከክርስቶስ ጋር መሞቱንና መቀበሩን በትንሣኤውም ባገኘው አዲስ ሕይወት ወደፊት ለመኖር ውሳኔውን የሚገልጽበት ምሳሌያዊ ድርጊት ነው፤ ሮሜ 6:3-6።

## ጥምቀት (2)

ሀ/ መጠመቅ የሚችል ሰው ማን ነው? መጠመቅ የሚችል ንስሐ ገብቶ በኢየሱስ አምኖ አዲስ ሕይወትን የተቀበለ ሰው ነው።

ለ/ አንድ ሰው መጠመቅ የሚችለው መቼ ነው?
1/ አንድ ሰው መጠመቅ የሚችለው ክርስቶስን የግል መድኃኒቱ አድርጎ በመቀበል ካመነ በኋላ ነው፤ የሐዋ.2:41፤ 8:36-38።
- ጳውሎስ ካመነ በኋላ ተጠመቀ፤ የሐዋ.9:18
- ወኅኒ ጠባቂው ካመነ በኋላ ተጠመቀ፤ የሐዋ.16:33።
2/ አንዳንድ ቤተ ክርስቲያኖች በውስጠ ደምባቸው የጥምቀትን ጊዜ የሚወስኑ ሕጎች አሉአቸው።
ለምሳሌ:-
- ትምህርት ሳይማር ቢጠመቅ የሚያደርገውን ስለማያውቅ ስለ ጥምቀት ትምህርት ከተሰጠው በኋላ መጠመቅ አለበት፤ ማቴ.28:19-20። «እያስተማራችኋቸው» ይላል፤ የሐዋ.8:35፤ 10:34-43።
- አንድ ሰው ከመጠመቁ በፊት አዲስ ሕይወትን ተቀብሎ የተለወጠ አረማመድ ማሳየት አለበት።

ሐ/ ጥምቀት የሰውን ነፍስ ሊያድን ይችላል? ጥምቀት የሰውን ነፍስ ሊያድን እንደማይችል ከዚህ በታች ከተጠቀሱት አሳቦች መረዳት እንችላለን።
1/ ሰው የሚድነው በክርስቶስ ባመነ ጊዜ ነው፤ የሚጠመቀውም ደኅንነትን አገኘቻለሁ ሲል ነው እንጂ ገና ለመዳን አይደለም። በጥምቀት መዳን ከተቻለ መጠመቅ የሰው ሥራ ስለሆነ ደኅንነት በሥራ ሆነ ማለት ነው። መዳን የሚቻለው ኢየሱስን በእምነት በመቀበል እንጂ በሥራ እንዳይደለ መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ቦታ ያስረዳል፤ ኤፌ.2:8-9፤ ዮሐ.1:12፤ የሐዋ.4:12።
2/ የወኅኒ ቤቱ ጠባቂ «እድን ዘንድ ምን ላድርግ?» ብሎ በጠየቀ ጊዜ ጳውሎስ:- «በክርስቶስ እመን» ብሎ መለሰለት እንጂ «ተጠመቅ» ብሎ አላዘዘውም፤ የሐዋ.16:31።

መ/ ሰው በጌታ ካመነ በኋላ ሳይጠመቅ ቢሞት ሊድን ይችላል? ከዚህ በታች የተጠቀሱት ምሳሌዎች ሰው ካመነ በኋላ ሳይጠመቅ ቢሞት ሊድን እንደሚችል ያሳያሉ።
1/ ከጌታ ጋር አብሮ የተሰቀለው ወንበዴ ሳይጠመቅ ዳነ፤ ሉቃስ 23:39-43።
2/ ማር.16:16 «ያላመነ ይፈረድበታል» እንጂ «ያልተጠመቀ ይፈረድበታል» አይልም።

ሠ/ ያመነ ሰው የሚጠመቀው በማን ስም ነው? ያመነ ሰው የሚጠመቀው በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ነው፤ ማቴ.28:19-20።

ረ/ ሰው ከተጠመቀ በኋላ በፍጹም ኃጢአት አይሠራም ማለት ነው? አይደለም፤ ሰው ከመጠመቁ በፊት ከኃጢአት የተለየ መሆን አለመሆኑ መመርመር አለበት፤ ከተጠመቀ በኋላ በአዲስ ሕይወት መመላለስ አለበት። ነገር ግን በኃጢአት ቢወድቅ ተናዞ ከጌታ ይቅርታን ማግኘት ይችላል። 1ዮሐ.1:9።

## ትምህርት 37

ጥያቄ 66:- የጌታ እራት ምንድነው?
መልስ:- የጌታ እራት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ እስኪመለስ ድረስ ለኛ ሲል ሥጋውን መቁረሱን እና ደሙን ማፍሰሱን የሚናስታውስበት ሥርዓት ነው፤ 1ቆሮ.11:26።

### የጌታ እራት (1)

ሀ/ የጌታ እራት ምንድነው?

1/ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመሞቱ በፊት በተያዘበት ማታ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር እራት ሲበላ ለመታሰቢያ የመሠረተው ሥረዓት ነው፤ ማቴ.26:26-28።

2/ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪመለስ ድረስ አማኞች የጌታን ሞት ለማስታወስ በአንድነት ተሰብስበው የሚካፈሉት እንጀረና ጽዋ ነው። እንጀረው በመስቀል ላይ የተቆረሰው የጌታ ሥጋ ምሳሌ ሲሆን ጽዋው ደግሞ በመስቀል ላይ ስለኛ ያፈሰሰው የደሙ ምሳሌ ነው፤ 1ቆሮ.11:23-25፤ ሉቃ.22:19-20።

3/ ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር የመተባበር ምልክት ነው፤ 1ቆሮ.10:16-17።

ለ/ የጌታን እራት የምንወስደው ለምንድነው?

1/ ክርስቶስ እንድንወስደው ትእዛዝ ስለሰጠን ነው፤ 1ቆሮ.11:24።

2/ የክርስቶስን ፍቅርና ያደረገልንን ሁሉ የምናስታውስበት መታሰቢያው ስለሆነ ነው፤ 1ቆሮ.11:24-25።

3/ በክርስቶስ ሞት ሕይወት እንዳገኘን በሰዎች ፊት ሞቱን የምንመሰክርበት ስለሆነ ነው፤ 1ቆሮ.11:26።

4/ ክርስቶስ ዳግመኛ ተመልሶ እንደሚመጣ በጥልቅ የምናስብበት ጊዜ ስለሆነ ነው፤ 1ቆሮ.11:26።

ሐ/ የጌታን እራት መውሰድ የሚችሉ እነማን ናቸው?

1/ በክርስቶስ አምነው የዳኑት ብቻ ናቸው፤ ላላመኑ ሰዎች ምንም ትርጉም ሊሰጣቸው አይችልም።

2/ የጌታን እራት የሚወስዱት አማኖች በክርስቶስ አምነው መዳናቸው ይበልጥ የተረጋገጠ እንዲሆን የተጠሙቁ ቢሆኑ ጸህና ነው። ስለዚህ አባልነትን በጥምቀት የሚወስኑ ቤተ ክርስቲያኖች ያልተጠመቁ ሰዎች በጌታ እራት ሥነ ሥርዓት እንዳካፈሉ ላይፈቅዱ ይችላሉ። በውስጠ ጸምባቸው የተወሰነ በመሆኑ ጸምባቸው የተከበረ መሆን አለበት።
3/ በማቴ.26:27 «ሁላችሁ ከርሱ ጠጡ» ስለሚል ይህን ሥርዓት መካፈል ያለባቸው አማኖች ሁሉ ናቸው።
4/ የጌታን እራት መውሰድ የሚችሉት በብርሃን የሚመላለሱ አማኞች ናቸው። ከእግዚአብሔርም ሆነ ከሌሎች አማኞች ጋር ያላቸውን ኅብረት ያቋረጡ አማኞች የጌታን እራት መውሰድ የለባቸውም፤ 1ቆሮ.11:28፤ 1ዮሐ.1:6።

## ትምህርት 38

## የጌታ እራት (2)

ሀ/ የጌታን እራት መውሰድ ያለብን እንዴት ነው? 1ቆሮ.11:28-31።
1/ ሁላችንም ብቃት የሌለን ሰዎች ነን። ብቃታችን ከኢየሱስ ስለተገኘ «እኔ ብቁ ነኝ» የሚል ትዕቢት ወይም «እኔ ብቁ አይደለሁም» የሚል ፍርሃት እንዲኖረን አያስፈልገም።
2/ የጌታን እራት ከመውሰዳችን በፊት ራሳችንን በመመርመር ያልተናዘዝነው ኃጢአት እንዳለ መናዘዝና የርስ በርስ ቂምም ካለ ማስወገድ ያስፈልገናል፤ 1ቆሮ.11:28።
3/ የጌታን እራት መውሰድ የሚያስፈልገን በልማድ እንደሚበላ ምግብ ሳይሆን በክብር የጌታን መከራ እያሰብን መሆን አለበት፤ 1ቆሮ.11:29።

ለ/ ሰው የጌታን እራት ሳይቀበል ራሱን መመርመር ያለበት ለምንድነው?
1/ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ስለሆነ ነው፤ 1ቆሮ.11:28።
2/ ሳይመረምር ቢወስድ ቅጣት፥ ድካም፥ መታመምና ሞት ስለሚያስከትልበት ነው፤ 1ቆሮ.11:30። ነገር ግን ሰው ራሱን መርምሮ ኃጢአቱን ሲናዘዝ ይቅርታን ስለሚያገኝ መውሰድ ይችላል፤ 1ዮሐ.1:9።

ሐ/ የጌታን እራት መውሰድ የዘላለም ሕይወት ይሰጣል? አይሰጥም።
1/ የጌታ እራት የክርስቶስ መታሰቢያ ነው እንጂ መድኃኒት አይደለም፤ 1ቆሮ. 11:24-25። የምንድነው ጌታ ኢየሱስን አምነን በመቀበል እንጂ ሰው በሚያደርገው ሥርዓት አይደለም። ስለዚህ የጌታን እራት መውሰድ እርሱ በመስቀል ላይ በፈጸመልን ጸኅነት

ላይ የሚታከል ተጨማሪ ጽድቅን አይሰጠንም።

2/ በዮሐ.6፡53-54 ላይ «ሥጋዬን የበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው» የሚለውን ቃል ብዙ ሰዎች በጌታ እራት መቀበል ስለሚተረጉሙት የጌታ እራት የሚያድናቸው ይመስላቸዋል። ጌታ በዚህ ቦታ ስለ ጌታ እራት አልተናገረም። ነገር ግን ምሳሌ እንደነበረ ጌታ ራሱ ተናግሮአል፤ ዮሐ.6፡60-63። ጌታ «የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም፥ በእኔ የሚያምን ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም» አለ፤ ዮሐ.6፡35። ስለዚህ ወደ እርሱ በእምነት ብንመጣ ለመንፈሳችን ምግብና መጠጥ አገኘተናል ማለት ነው። ወደ እርሱ መጥተን ባናምነበት ግን የዘላለምን ሕይወት አናገኝም። በዮሐንስ 6 ጌታ የተናገረው በእርሱ እምነን የዘላለምን ሕይወት እንደምናገኝ እንጂ በፍጹም ስለ ጌታ እራት አልተናገረም። በዚያን ጊዜ ጌታ የተናገረው ላላመኑ ሰዎች እንጂ ላመኑት አልነበረም፤ ያላመኑ ሰዎችም የጌታን እራት ምንነት ያልተረዱ ስለሆኑ ጥቅሱ የጌታን እራት እንደሚያመለክት ተደርጎ መወሰድ የለበትም።

መ/ እንጀራውና ጽዋው ወደ ክርስቶስ ሥጋና ደም ይለወጣል?
አይለወጥም፤ በማቴ.26፡21 «ይህ ሥጋዬ ነው» ብሎ እንዳስተማረ፥ በዮሐ.10፡9፤ 15፡1 ውስጥ እንዲሁ «እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ» «በሩ እኔ ነኝ» ብሎ አስተምሮአል። እነዚህ ሁሉ ስለጌታ ለመማር የሚረዱን ምሳሌዎች ናቸው እንጂ ጌታ የወይን ግንድ ወይም በር አይደለም። ክርስቶስ «ይህ ደሜ ነው» ብሎ ሲናገር የጌታ እራት እሱ ሞቶ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ለሞቱ መታሰቢያ እንደሚሆን ለማስተማር ያህል ተናገረ እንጂ ጽዋው ደም አልነበረም። በዚያን ሰዓት ደሙ ገና አልፈሰሰም።

## ትምህርት 39

ጥያቄ 67፡- ጌታችን ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ለቤተ ክርስቲያን በመጨረሻ የሰጠው ትእዛዝ ምንድነው?

መልስ:- ጌታችን ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ለቤተ ክርስቲያን በመጨረሻ የሰጠው ትእዛዝ ቤተ ክርስቲያን ለዓለም ሁሉ የክርስቶስን ወንጌል እንድታስተምርና አማኞችን ደቀ መዛሙርት እንድታደርግ ነው፤ ማር.16፡15፤ የሐዋ.1፡8፤ ማቴ.28፡19-20።

የክርስቶስ የመጨረሻ ትዕዛዝ

ሀ/ ማር.16፡15 ፡-

